ለድንገተኛ ጊዜ አደጋ ዝግጁ መሆን፡-
ለስደተኞች የሚሆን መመሪያ

ይህንን በራሪ ወረቀት ያንብቡ እና በቅርብ በሚያገኙበት ቦታ ላይ ያስቀምጡ

ADMINISTRATION FOR CHILDREN & FAMILIES

የስደተኞች ዳግም ሰፈራ ቢሮ
የሰው ልጅ አገልግሎቶች ቢሮ የድንገተኛ አደጋ ዝግጁነት እና ምላሽ

Photo coutesy UNHCR

ቋሚህውሮህሬሀ ገሬሚዋተ

ለተጨማሪ መረጃ፡-

ፌዴራል አስቸኳይ አስተዳደር ኤጀንሲ (FEMA) – www.ready.gov
አሜርካ ቀይ መስቀል (American Red Cross) - www.redcross.org

የአገር ሁኔት እርዳታ መስመር (Disaster Distress Helpline) – www.disasterdistress.samhsa.gov/
የሚያውቁት ሰው አገርዎ ከደረሰበት እና እርዳታ የሚያስፈልገው ከሆነ አስቸኳይ አመረጃ፡ ድርጅት፡ እና ምክር የአገር ሁኔት ነጻ የእርዳታ መስመር 1-800-846-8517 ይደውሉ። የማስተርጎም አገልግሎ አለ።

ድንገተኛ አደጋ *የምንለው በጤንነት፣ በህይወት ወይም በንብረት ላይ ድንገተኛ አደጋ በሚከሰት ጊዜ ነው።*

9-1-1
ደንገተኛ አደጋ

እንደ የእሳት አደጋ፣ ዝርፊያ፣ ወይም ከባድ የጤንነት ችግር (ለምሳሌ፣ አለመተንፈስ፣ ራስን መሳት፣ ወይም የማያቋርጥ ደም መድማት) ያለ የድንገተኛ አደጋ በሚኖር ጊዜ፣ ከማንኛውንም ስልክ ላይ ወደ **9-1-1** *ይደውሉ። ምን አይነት የድንገተኛ አደጋ እንዳለ ይንገሩዋቸው፣ ከዚያም እንደ ፓሊስ፣ የእሳት አደጋ ማጥፊያ፣ ወይም አንቡላንስ ያሉትን አግባብ ያላቸውን እገዛ ያገኛሉ። መደወሉን አያዘግዩ፣ እንግሊዝኛ የማይናገሩ ቢሆንም እንኳን፣ ለእርስዎ የሚሆን እገዛን ማግኘት ይችላሉ።*

ከግላዊ ድንገተኛ አደጋዎች በተጨማሪ፣ ከፍተኛ የሆኑ የድንገተኛ አደጋዎች በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ በሆኑ ችግሮች ሊከሰት ይችላል። በርካታ ከፍተኛ አደጋዎች ሙቀት፣ ሃይል እና የመገናኛ አገልግሎቶችን ሊያበላሹ ይችላሉ።

ከዚህ በታች በተፈጥሮ የሚከሰቱ አደጋዎች በጥቂቱ ተዘርዝረዋል - እንዲሁም አደጋዎቹ በሚከሰቱ ጊዜ እራስዎን እና ቤተሰብዎን ለመጠበቅ የሚያደርጉዋቸው ጥቂት ፍንጮችም ተቀምጠዋል። የተፈጥሮ አደጋዎች ሌሎች ምሳሌዎች ጎርፍ፣ የዱር እሳት ሰደድ፣ ከፍተኛ ሙቀት፣ እና የመሬት መንሸራተትን ያካትታሉ። በሚከተለው ድረ ገፅ ላይ የበለጠ ይወቁ፡-
http://www.ready.gov/natural-disasters

ቶርኔዶ፡- በመሬት ላይ የሚከሰት በጣም ጠንካራ የንፋስ ማዕበል ሲሆን ከሰማይ ላይ የቱቦ ቅርፅ መሳይ ጉም ወደ ምድር ይወርዳል። ቶርኔዶ ህንፃዎችን ሊያወድም ይችላል።

- እርስዎ ያሉበት አካባቢ ቶርኔዶ እንደሚያሰጋው ማስጠንቀቂያ ከደረስዎ፣ በአስቸኳይ መጠለያ ይጠይቁ!
- በህንፃ ውስጥ ካሉ ወደ ዝቅተኛው ወለል ይሂዱ፣ ከመስኮቶች እና በሮች ይራቁ።
- በርካታ ጉዳቶች የሚከሰቱት በአየር ላይ በሚበሩ ስብርባሪች ነው፣ ስለዚህ ራስዎን ይጠብቁ ።

ለጎረቤቶችዎ እርስዎ ደህና እንደሆኑ ለማሳወቅ ይህንን በመስኮት ላይ ያስቀምጡ

OK

ለጎረቤቶችዎ እገዛን እንደሚፈልጉ ለማሳወቅ ይህንን በመስኮቱ ላይ ያስቀምጡ

HELP

የመሬት መንቀጥቀጥ ፦ ድንገተኛ የምድር መነዋወጥ። የመሬት መንቀጥቀጥ ምድር እንዲሰነጠቅ ያደርጋል እና ህንፃዎች ሊፈርሱ ይችላሉ።

- በቤት ውስጥ ከሆኑ፣ መሬት ላይ ይተኙ፣ ጠንካራ በሆነ ጠረጴዛ ስር በመሆን ሽፋን ያግኙ፣ እና መንቀጥቀጡ እስኪያበቃ ድረስ ይያዙ።
- ከቤት ውጭ ከሆኑ፣ መንቀጥቀጡ እንኪያቆም ድረስ በክፍት ስፍራ ላይ ይቆዩ። ከህንፃዎች፣ ከመንገድ መብራቶች እና ከኤሌክትሪክ ገመዶች ላይ ይራቁ።

ሃሪኬን ፦ በከፍተኛ ንፋስ፣ በከባድ ዝናብ እና ረዥም ሞገድ ላይ የሚከሰቱ ማዕበሎች። ከሃሪኬይን የሚከሰት ንፋስ እና ጎርፍ ህንፃዎችን ሊያጠፉ ይችላሉ።

- ሃሪኬይን የሚከሰት ከሆነ፣ ምን ማድረግ እንደሚቸሉ መረጃን ለማግኘት በራዲዮ ወይም ቲቪ ያዳምጡ/ይመልከቱ ወይም ኢንተርኔት ላይ ይመልቱ።
- በቤት ውስጥ ይቆዩ፣ ከመስኮቶች እና በሮች ይሸሹ
- በአካባቢው ባሉ ባለስልጣናት ስፍራውን አንዲለቁ ከተነገርዎ መልቀቅ አለብዎ

የበልግ ማዕበል እና ከባድ ብርድ ፦ በርካታ በረዶ፣ በጣም ዝቅተኛ የአየር ንብረቶች፣ ከባድ ንፋስ፣ እና በረዶ።

- በማዕበሉ ጊዜ በቤት ውስጥ ይቆዩ ።
- ደረቅ መሆንዎን ያረጋግጡ። ምክንያቱም ርጥብ ልብሶች የሰውነት ሙቀት መቀነስን ያስከትላሉ።
- በርዶአማ መንገዶች የመኪና አደጋን ስለሚያስከትሉ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር አይንዱ።
- ቤቱን ለማሞቅ ስቶቭ አይጠቀሙ

ከዚህ በታች የሰው ሰራሽ አደጋዎች ምሳሌዎች ናቸው — እና ራስዎን እና ቤተሰብዎን ለመከላከል ማድረግ ስለሚገባዎ ነገር ጥቂጥ ፍንጮች። ሌሎች ምሳዎች፣ የኒውክለር ሃይል ማመንጫ አደጋዎች፣ ፍንዳታዎች፣ የሽብርተኛ ትቃቶች። ከዚህ ቀጥሌካለው ድረ ገፅ ተጨማሪ ነገር ይወቁ፡- http://www.ready.gov/accidental-emergencies

ጎጂ የኬሚካል ውጤቶች ፡- ጥቂት ኬሚካሎች ህንፃዎችን ሊያበላሹ ይችላል እና በድንገት ከጥንቃቄ ውጭ ከተለቀቁ ለጤንነትም ጎጂ ሊሆኑ ይችላሉ። ፍንዳታ ሊኖር ይችላል፤ በሌላ በኩል፣ እርስዎ ኬሚካሉን ለማየት ወይም ለማሽተት አይችሉ ይሆናል።

- ምን ማድረግ እንዳለብዎ ራዲዮ ወይም ቴሌቪዥን ያዳምጡ/ይመልከቱ አልያም ኢንተርኔት ላይ ይመልከቱ።
- በአካባቢው ባለስልጣናት ያሉበትን ቦታ ለቀው እንዲቀሳቀሱ ከተጠየቁ ይንቀሳቀሱ ።
- ከቤት ውስጥ እንዳይወጡ ከተጠየቁ፣ ሁሉንም መስኮቶች እና በሮች ይዝጉ እና ከቤት አይውጡ። ማንኛውም ወደ ውጭ የሚያስወጣ ክፍተትን ያሽጉ።

የቤት ቃጠሎዎች፡- በየእለቱ፣ አሜሪካውያን፣ የቤት ቃጠሎዎች ያጋጥሟቸዋል። ቃጠሎ በፍጥነት ይዛመታል እና ለማምለጥ የሰከንድ ጊዜያት ሊሆን ይችላል የሚኖርዎ።

- በቤት ውስጥ ያለው የጭስ መርማሪ ድምፅ በሚያሰማ ጊዜ፣ በፍጥነት ይውጡ።
- ጭስ ካለ፣ ለመውጣት በጭሱ ስር ቀስ ብለው ይለፉ።
- ልብስዎ እሳት ከያዘ፣ ወደ መሬት ላይ ይጣሉት፣ ፊትዎን በእጆችዎ ይሸፍኑ፣ እና እሳቱ እስኪጠፋ ድረስ ይሽከርከሩ። ወዲያውኑ የህክምና እርዳታን ያግኙ።
- መውጣት ካልቻሉ፣ በር ይዝጉ እና መውጫውን ይፈትሹ እንዲሁም ከበሩ ስር ያሉ ስንጥቆችን በማሸፈን ጭሱ እንዲወጣ ያድርጉ። ወደ 9-1-1 ይደውሉ እና የት እንዳሉ ይንገሩዋቸው።

የካርቦን ሞኖክሳይድ ብክለትን ይከላከሉ!

በአደጋዎች ጊዜ፣ ቤትዎ ኤሌክትሪክ ላይኖር ይችላል። ይህ ገጽ ያለ ኤሌክትሪክ ቤትዎን ማሞቅና ምግብ ማብሰል እንዴት ለካርቦን ሞኖክሳይድ እንደሚያጋልጥና እራሰዎን ለመጠበቅ ምን ማድረግ እንዳለብዎ ያብራራልዎታል።

ካርቦን ሞኖክሳይድ ልናየው፣ ለናሽተው ወይም ልንቀምሰው የማንችለው ጋዝ ነው ሆኖም ግን ጎጂ ነው — ሞትንም ሊያስከትል ይችላል — በብዛት ከተነፈስነው። ካርቦን ሞኖክሳይድ ነዳጅ በማቃጠል ይፈጠራል። ነዳጅ በቤት ውስጥ ማቃጠል ካርቦን ሞኖክሳይድ በቤት ውስጥ እንዲጠረቃም ሊያደርግ ይችላል፣ ገዳይም ሊሆን ይችላል።

- በፍጹም ቤት ለማሞቅ የጋዝ ምድጃ አይለኩሱ።
- በፍጹም በቤት ውስጥ በከሰል ወይም ጋዝ ምግብ አያብስሉ።
- በፍጹም ተንቀሳቃሽ ጀነሬተር በቤት ውስጥ፣ በጋራጅ ውስጥ፣ በመኪና ማቆሚያ ውስጥ አይጠቀሙ። ተንቀሳቃሽ ጀንሬተር ጋዝ የሚያቀጣጥል መብራት በማይኖርበት ጊዜ የተወሰኑ በኤሌክትሪክ መሳሪያዎች የሚያንቀሳቅስ መሳሪያ ነው።
- ጀነሬተሮችን ከቤት ወጪ ወይም ከተከፈቱ መስኮቶች እና የአየር ማስተላለፊያዎች ራቅ አድርገው ብቻ ይጠቀሙ።
- ያለሚሰራ የጭስ ማውጫ አያቀጣጥሉ።
- ቤትዎ የሚሰራ የካርቦን ሞኖክሳይድና ጢስ መቆጣጠሪያዎች መኖሩን ያረጋግጡ

የካርቦን ሞኖክሳይድ ብክለት ስሜቶች፡-
ራስምታት፣ ድካም፣ የመተንፈስ ችግር፣ መፍዘዝ፣ ማቅለሽለሽ።

የካርቦን ሞኖክሳይድ ብክለት አጋጥሞኛል ብለው ካሰቡ፡-
ቤቱን ለቀው ይውጡና ትኩስ አየር ያግኙ። የህክምና እርዳታ ያግኙ።

መጥፎ ነገር ከተከሰተ

የቤተሰብ አባልዎን ጉዳት እንደደረሰባቸው ይፈትሹ፡-

- አንድ ሰው በጣም እየደማ ከሆነ፣ የደም መፍሰሱን ለማቆም፣ የሚቻል ከሆነ፣ ቁስሉን ተጭነው ይዘው አካሉን ከፍ ያድርጉ።
- ሰውየውን ያረጋጉና ደህንነታቸውን ይጠብቁ።
- ሰወየው እንዳይበርዳቸው ያድርጉ።
- ለእርዳታ 9-1-1 ይደውሉ።

ቤትዎን መንከባከብ፡-

- ዜና ለመከታተል ሬዲዮ ያዳምጡ ቲቪ ይመልከቱ ወይም በይነመረብ ይጎብኙ።
- አንስተኛ እሳቶችን ተንቀሳቃሽ የእሳት ማጥፊያ ተጠቅመው ያጥፉ።
- ከአደጋ በፊት ውሃ፣ ኤሌክትሪክ እና ጋዝ እንዴት እንደሚጠፉ ይማሩ።
  - በአደጋ ጊዜ የውሃ አቀርቦቱ ሊበከል ይችላል። ወደቤትዎ የሚገባውን ውሃ ባልስልጣኖች ለመጠጥ ደህንነቱ የተጠበቀ ነው እስኪሉ ድረስ ይዝጉት።
  - ብልጭታዎች ከተመለከቱ ኤልክትሪኩን ከዋናው የኤሌክትሪክ መቆጣጠሪያ ወይም ከፊውዝ ሳጥኑ ያጥፉ።
  - ያፈተለከ ጋዝ ፍንዳታ ሊያስከትል ይችላል። ጋዙ የሚያፈተልክ ከሆነ እንደበሰበሰ እንቁላል ይሸታል። ጋዝ ከሸተትዎት፣ የሚነፍስ ወይም የሚያፋጭ ድምጽ ከሰሙ መስኮቱን ይከፈት ይተውት እና ይውጡ። ከጉረቤት ሆነው የጋዝ ኩባንያው ጋር ይደውሉ። ጋዙን አጥፈተውት ከሆነ መልሶ ማብራት ያለበት ጋዝ ኩባንያው ብቻ ነው።

በመጀመር ላይ

ቀድሞ በማቀድ አደጋዎች ከመከሰታቸው በፊት ዝግጁ መሆን ይቻላል። እርዳታ እስኪመጣ ድረስ ምን ማድረግ እና ወዴት መሄድ እንዳለባችሁ እንድታውቁ እራስዎን እና ቤተሰብዎን ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። የሚቀጥሉት ጥቂት ገጾች እንዴት ዝግጁ እንደሚሆኑ እና ደህንነትዎን እንደሚጠብቁ ፍንጮች ይሰጥዎታል።

በሚኖሩበት ቦታ ምን አይነት አደጋዎች ሊከሰተ እንደሚችሉ ይወቁ። ለእያንዳንዱ እንዴት መዘጋጀት እንደሚችሉ መረጃ ያግኙ። ከአደጋው በፊት፣ በአደጋው ጊዜ እና ከአደጋው በኋላ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ከቤተሰብዎ አባላት ጋር ይወያዩ። የአደጋ ጊዜ መውጫዎች እና የእሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በቤትዎ/በህንፃዎ ውስጥ የት እንደሚገኙ ሁሉም ሰው ማወቁን ያረጋግጡ።

በአደጋው ጊዜ እርስዎ እና ቤተሰብዎ ከተለያዩ እና ወደቤትዎ መመለስ ካልቻሉ የት እንደሚገናኙ ይወያዩ። የመገናኛ ቦታውን እዚህ ጋር ይጻፉ፡- _____

ቤትዎ ውስጥ መቆየት ካልቻሉ ሊያቆይዎ የሚችሉ ጓደኞችዎን፣ ዘመዶችዎን፣ ወይም ሰፖንሰሮችን ያስቡ።
መረጃዎን እዚህ ይጻፉ፡-
ስም፡- _____ ስልክ፡- _____ አድራሻ፡- _____

ከአንዳንድ አደጋዎች በኋላ የአደጋ ጊዜ መጠለያዎች ሊዘጋጁ ይችላሉ። ወደመጠለያ መሄድ እንዳልብዎ ከብዙሃን መገናኛ ወይም ከጓደኞችዎ ይረዱ።

አደጋው ከፍተኛ ከሆነ እና ብዙ ሰው የተጎዳ ከሆነ፣ የአደጋ ጊዜ ሰራተኞች ወዲያውኑ ሊረድዎ አይችሉ ይሆናል። እንደአደጋው መጠን እራስዎን እና ቤተሰብዎን እየረዱ ቢያንስ ለ4 እና ከዚያ ለሚበልጡ ቀናት መቆየት ሊኖርብዎ ይችላል።

መዘጋጀት፡-

በቤት ውስጥ ለመቆየት የአደጋ ጊዜ ቋት ያዘጋጁ

ለአደጋ ጊዜ በቤት ውስጥ በአንድ ቦታ መኖር ያለባቸው ነገሮች፡-

- ☐ የመጀመሪያ እርዳታ ሳጥን (ባንዴጆች፣ ጸረ ተዋሃሲያን ቅባት፣ መቀሶች፣ ቲዊዝርስ፣ ጎዝ ፓድስ እና ጥቅሎች፣ ጸረ ባክቴሪያ መጥረጊያዎች)

- ☐ ባትሪ - በቁልፍ የሚሰራ ወይም በእጅ በመዘወር የሚነሳ ሬድዮ (ምናልባት መብራት የሚጠፋ ከሆነ)

- ☐ የእጅ ባትሪዎች እና ባትሪ ድንጋዮች

- ☐ ፊሽካ ለእርዳታ ምልክት ለመስጠት

- ☐ የፕላስተር ጥቅል (Duct tape)

- ☐ ወረቀት እና እርሳስ/ብእሮች

- ☐ መድሃኒቶች

- ☐ ጠንካራ ጨማዎች እና ጓንቶች

- ☐ በሚገባ በጣሳ ውስጥ የታሸገ/ደረቅ ምግብና የጣሳ መክፈቻ

- ☐ የህጻናት አቅርቦቶች

- ☐ የቆሻሻ ከረጢቶች እና የህጻናት መጥረጊያዎች/ቲሹ/ የወረቀት ፎጣዎች ንህጽናን ለመጠበቅ

- ☐ መፍቻ ቧንቧዎችን ለመዝጋት

- ☐ ተጨማሪ ገንዘብ

ቢያንስ ለ4 ቀናት የሚሆን በቂ ምግብና መጠጥ ማኖር፡-

- አንድ ጋሎን ውሃ በሰው በየቀኑ ያስፈልጋል።
- በቤተሰባችን ውስጥ _____ ሰው አለ x 4 ቀናት = _____ ጋሎን ውሃ ያስፈልጋል።

አስፈላጊ ሰነዶች

አስፈላጊ ሰነዶችዎ የት ቦታ እንደሚቀመጡ ይወቁ። አንድ ቦታ ላይ ማስቀመጥ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

ቤትዎን መልቀቅ ካልብዎ እነዚህን ሰነዶች ይዘው ለመወጣት ዝግጁ ያድርጉ።

- ☐ የልደት ምስክር ወረቀት/I-94 ቅጽ
- ☐ ፓስፖርት/የመንጃ ፈቃድ/ሎሎች ፎታ ያላቸው መታወቂያዎች
- ☐ የማህበራዊ ዋስትና ካርዶች
- ☐ የመድህን ዋስትና ካርዶች
- ☐ የ ATM/ክሬዲት ካርዶች ቅጂና የባንክ መረጃ
- ☐ የ ንብረቶች/ሞርጌጅ ቅጂዎች
- ☐ የቅርብ ጊዜ የታክስ ተመላሽ
- ☐ የክትባት መዝገቦች
- ☐ ሌሎች ሰነዶች፡- (ይዘርዝሯቸው)

_____

_____

አስፈላጊ ስሞች እና ስልክ ቁጥሮች

- የቤት ስልክ ቁጥር፣ የቤተሰብ አባል የተንቀሳቃሽ ስልክ ቁጥር፡- _____
  _____
- ሥራ፡- _____
- ርፋማሲ፡- _____
- መሪ መጀመሪያ/የህጻናት እንክብካቤ፡- _____
- ትምህርት ቤት፡- _____
- የመሬት ባለቤት/ሞርጌጅ ኩባንያ፡- _____
- ቤት/የኪራይ መድህን፡- _____
- የተሽከርካሪ መድህን፡- _____
- ኤሌክትሪክ ኩባንያ፡- _____
- ጋስ ኩባንያ፡- _____
- ውሃ ኩባንያ፡- _____
- የከተማ መረጃ፡- _____
- አውቶብስ/የመጓጓዣ መረጃ፡- _____
- ሃይማኖታዊ እውቂያ፡- _____
- ዘመዶች፡- _____
- ጓደኞች፡- _____
- የሰፈራ ኤጀንሲ፡- _____
- የጉዳይ ሰራተኛ፡- _____

ዝግጁ በመሆን ላይ፡-

ለመሄድ የአስቸኳይ ጊዜ ቋት ያዘጋጁ

ቤትዎን ለቀው መሄድ ቢኖርብዎ ዝግጁ የሚያደርጓቸው ነገሮች፡-

- ☐ መድሃኒቶች (የሃኪሀም ማዘዣ እና ከመደርዲሪያ ላይ)
- ☐ የህክምና መሳሪያዎች
- ☐ ተንቀሳቃሽ ስልኮች እና የሃይል መሙያዎች
- ☐ የግል ንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች (የጥርስ ቡሩሽ፣ የጥርስ ሳሙና፣ የጸጉር ማበጠሪያ)
- ☐ የአይን መነጽር፣ ኮንታክትስ፣ ዴነቱርስ
- ☐ ለእርምጃ ምቹ ጫማዎች
- ☐ ተለዋጭ ልብሶች
- ☐ ለዝናብ የሚሆኑ ቁሳቁሶች
- ☐ አሻንጉሊት ወይም ጨዋታ ለልጆች
- ☐ የምቾት ቁሳቁሶች (ስናክስ፣ የተጠቀጠቁ እንስሳት፣ መጽሃፍ)
- ☐ ገንዘብ እና የቼክ ደብተር
- ☐ አስፈላጊ ሰነዶች
- ☐ ቁልፍች



ልዩ ቁሳቁሶች ለህጻናት እና ታዳጊ ልጆች፡-

- ☐ ጡጦዎች
- ☐ ዲይፐሮች
- ☐ የህፃናት ፎርሙላ፣ የህጻናት ምግብ፣ ቢብስ
- ☐ የልጆች መጥረጊያ (ቤቢ ዋይፕስ)
- ☐ የቆሻሻ መጣያ ቀረጢት
- ☐ የዳይፐር ሽፍታ ቅባት
- ☐ የህጻናት ጸረ-ትኩሳት መድሃኒቶች/ስሪንጆች
- ☐ ቴርሞሜትር
- ☐ ፔስፋየር (Pacifier)
- ☐ የህጻናጽ ብርድልብስ
- ☐ የእጅ ማጽጃ (Hand sanitizer)

የህክምና መረጃ ለእያንዳንዱ ቤተሰብ

ለእያንዳንዱ የቤተሰብዎ አባል የህክምና መረጃ ይሙሉ፣ ስለዚህም ይህ መረጃ በተገቢዎ ቦታ ይኖርዎታል። በአስቸኳይ ጊዜ የጤና እንክብካቤ አቀራቢዎን ለማገኘት ከዚህ ማጣቀስ ይችላሉ፣ ወይም እርስዎ ወይም የቤተሰብዎ አባል የህክምና እርዳታ ካስፈለግዎ ይህንን ለአስቸኳይ ወይም የጤና እንክብካቤ ሰራተኛ ያሳዩ።

- ስም፡- _____
- ሃኪም/ክሊኒክ፡-_____
- ስልክ፡- _____
- የመድህን አይነት እና ቁጥር፡- _____

_____

አላርጂዎች፡- _____

የህክምና ሁኔታዎች፡- _____

_____

አሁን የሚጠቀሟቸው መድሃኒቶች፡- _____

_____

- ስም፡- _____
- ሃኪም/ክሊኒክ፡-_____
- ስልክ፡- _____
- የመድህን አይነት እና ቁጥር፡- _____

_____

አላርጂዎች፡- _____

የህክምና ሁኔታዎች፡- _____

_____

አሁን የሚጠቀሟቸው መድሃኒቶች፡- _____

_____

- ስም፡- _____
- ሃኪም/ክሊኒክ፡-_____
- ስልክ፡- _____
- የመድህን አይነት እና ቁጥር፡- _____

_____

አላርጂዎች፡- _____

የህክምና ሁኔታዎች፡- _____

_____

አሁን የሚጠቀሟቸው መድሃኒቶች፡- _____

_____

የህክምና መረጃ ለእያንዳንዱ ቤተሰብ

- ስም፡- _____
- ሃኪም/ክሊኒክ፡-_____
- ስልክ፡- _____
- የመድህን አይነት እና ቁጥር፡- _____

_____

አላርጂዎች፡- _____

የህክምና ሁኔታዎች፡- _____

_____

አሁን የሚጠቀሟቸው መድሃኒቶች፡- _____

_____

_____

- ስም፡- _____
- ሃኪም/ክሊኒክ፡-_____
- ስልክ፡- _____
- የመድህን አይነት እና ቁጥር፡- _____

_____

አላርጂዎች፡- _____

የህክምና ሁኔታዎች፡- _____

_____

አሁን የሚጠቀሟቸው መድሃኒቶች፡- _____

_____

_____

- ስም፡- _____
- ሃኪም/ክሊኒክ፡-_____
- ስልክ፡- _____
- የመድህን አይነት እና ቁጥር፡- _____

_____

አላርጂዎች፡- _____

የህክምና ሁኔታዎች፡- _____

_____

አሁን የሚጠቀሟቸው መድሃኒቶች፡- _____

_____

_____